መልእክት ሦስት

## ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መጠናቀቅ
## በእውነት መቀናበር እና
## ለእውነት መንገድ እና ለእውነት መሰራጨት
## ፍጹም መሆን

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዮሐ. 8፡12፣ 32፤ 1 ዮሐ. 1፡5-8፤ 3 ዮሐ. 3-4፣ 8፤ 1 ጢሞ. 2፡4፤ 4፡3

**I. በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ውጥን ለክርስቶስ አካል፣ ለቤተ ክርስቲያን መቀናበር በሂደት ያለፈውን እና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ ለመግለጥ በእግዚአብሔር ወደ ተመረጡት አማኞቹ ውስጥ ክርስቶስን ከብልጥግናዎቹ ሁሉ ጋር ማደል ነው—ኤፌ. 3፡8-10።**

**II. ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መጠናቀቅ በእውነት መቀናበር ያስፈልገናል—1 ዮሐ. 2፡4፤ 2 ዮሐ. 1-2፦**

ሀ. በእውነት መቀናበር ማለት የመለኮታዊው መገለጥ ውስጠ-መሠረታዊ ንጥረ-ነገር የማንነታችን ክፍል፣ ውስጠ-መሠረታዊ ማንነታችን፣ ሕይወታዊ ቅንብራችን ይሆን ዘንድ በውስጣችን መሠራቱ ነው—1 ዮሐ. 1፡8፤ 4፡6፤ 5፡6።

ለ. ወደ ውስጣችን የሚቀናበረው የተደላደለ እውነት በእኛ ውስጥ የማያቋርጥ እና የረጅም ጊዜ ምግብ ይሆናል—1 ጢሞ. 4፡6።

ሐ. እውነቱ ወደ ውስጣችን ከተሠራና ወደ ማንነታችን ውስጥ ከተቀናበረ፣ የእግዚአብሔርን የመለኮትነቱን ብልጥግናዎች ፍላጎት እና በመጠናቀቁ ያገኛቸውን ነገሮች ፍላጎት መጠበቅ እንችላለን—ራእ. 21፡12፣ 17።

መ. እያንዳንዱ የዳነ ሰው የእውነቱ—በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጡት እውነተኛ ነገሮች—ሙሉ ዕውቀት፣ ሙሉ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል—1 ጢሞ. 2፡4፤ 4፡3፤ 2 ጢሞ. 2፡25፤ 3፡7።

ሠ. የእውነቱ ሙሉ እውቀት የእውነቱ ጥልቅ-ዝርዝር ግንዛቤ፣ በእምነት የተቀበልናቸው የመንፈሳዊ እና የመለኮታዊ ነገሮች እውነታ ሙሉ እውቅና እና አድናቆት ነው—ቲቶ 1፡1፤ 2 ተሰ. 2፡13።

ረ. የጌታ ቃል፣ የጌታ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ተገቢ ፍቺ ይጠይቃል፤ ለዚህ የሕይወት-ጥናቶች መጽሐፍት አሉን—2 ጢሞ. 2፡15።

ሰ. እውነቶቹን ለመማር ዋጋ መክፈል አለብን—ምሳ. 23፡23፦

1. ጌታ የሚናገረውን እና የሚፈልገውን ለማወቅ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ውስጥ መግባት ያስፈልገናል—ዮሐ. 8፡12።
2. ምንም ነገር የመፍጠር መብት የለንም፤ ይልቁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ፈልገን እናገኛለን።
3. እውነትን ከተማርን በኋላ ጌታ የእኛ እውነታ ይሆን ዘንድ ክርስቶስን መለማመድ አለብን፤ በዚህ መንገድ ሰዎችን ስናነጋግር እውቀት ወይም አስተምህሮ አንሰጣቸውም፣ ነገር ግን ክርስቶስን ለእነርሱ እናገለግላለን—ኤፌ. 3፡16-17፤ 4፡15፣ 21።

ሸ. እጹብ-ድንቅ ወደሆነው የአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ እውነት ውስጥ ጠልቆ ለመግባት የመለኮታዊውን እውነት ውጫዊ ገጽታ ብቻ በቀላሉ አይቶ ከማለፍ አርነት መውጣት እና ከጌታ ጋር አብረን በመትጋት መተባበር አለብን—3፡9።

ቀ. በእውነት የተቀናበሩ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ በረከት ናቸው—ሮሜ 9፡1፤ 15፡29።

**III. ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መጠናቀቅ፣ ለመለኮታዊው እውነት መንገድ ፍጹም መሆን ያስፈልገናል—2 ጴጥ. 2፡2፦**

ሀ. የእውነት መንገድ የአዲስ ኪዳን ይዘቶች እውነታ በሆነው በእውነቱ መሠረት የሆነ የክርስቲያን ሕይወት መንገድ ነው—ቁ. 2።

ለ. የእውነት መንገድ ቀጥተኛ መንገድ ነው፤ ቀጥተኛውን መንገድ መውሰድ ያለ ጠማማነት እና ያለ ወገንተኝነት ቅን ሕይወት መኖር ነው—ቁ. 15።

ሐ. የእውነት መንገድ የጽድቅ መንገድ ነው፤ የጽድቅን መንገድ መውሰድ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ትክክል የሆነን ሕይወት፣ ለእግዚአብሔር የጽድቅ መንግሥት በጽድቅ መሠረት የእግዚአብሔርን አገዛዛዊ ፍርድ መቀበል የሚችል ሕይወት መኖር ነው—ቁ. 21፣ 9፤ ማቴ. 5፡20፤ ሮሜ 14፡17።

መ. በእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ውስጥ የጌታን ሙሉ ድነት በማሳየት የእውነት መንገድ "መንገዱ" ነው—ሐዋ 9፡2፦

1. በክርስቶስ ቤዛነት እና በመንፈስ መቀባት በኩል ወደ አማኞቹ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን የሚያድልበት መንገድ ነው—ኤፌ 1፡7፤ 1 ዮሐ. 2፡27።
2. አማኞች እግዚአብሔርን የሚካፈሉበት እና እግዚአብሔርን የሚደሰቱበት መንገድ ነው—2 ጴጥ. 1፡4።
3. አማኞች እግዚአብሔርን በመደሰት በመንፈሳቸው እርሱን የሚያመልኩበት እና ከተሰደደው ክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን የተሰደደውን ክርስቶስ የሚከተሉበት መንገድ ነው—ዮሐ. 4፡24፤ ዕብ. 13፡12-13።
4. አማኞች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚመጡበት እና የኢየሱስን ምስክር ለመሸከም ወደ ክርስቶስ አካል ውስጥ የሚገነቡበት መንገድ ነው—1 ቆሮ. 1፡2፤ 12፡27፤ ራእ. 1፡2።

ሠ. የእውነትን መንገድ መውሰድ ለእውነቱ በመታዘዝ ነፍሳችንን ማንጻት ነው፤ ይህ የእግዚአብሔር የእውነታ ቃል የሆነው የሚቀድሰው እውነት ነው—1 ጴጥ. 1፡22፤ ዮሐ. 17፡17፦

1. ለእውነት በመታዘዝ የነፍሳችን መንጻት እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፣ በሙሉ ነፍሳችን እና በሙሉ አእምሯችን እንወደው ዘንድ መላው ማንነታችንን ለእግዚአብሔር ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል—ማር. 12፡30።
2. እንዲህ ያለው የነፍሳችን መንጻት ግብዝነት የሌለበትን የወንድማማቾችን መዋደድ፣ ማለትም እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ከልብ አጥብቆ መውደድን ያመጣል—1 ዮሐ. 5፡1።

## IV. ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መጠናቀቅ ለመለኮታዊው እውነት መሰራጨት ፍጹም መሆን ያስፈልገናል—ማቴ. 24፡14፤ 28፡19፦

ሀ. ወንጌል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን እውነቶች በሙሉ ያካትታል፤ መላው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ወንጌል ነው—ኤፌ. 1፡13፤ ቆላ. 1፡15፦

1. ዛሬ የቤተ ክርስቲያን ልዩና ብቸኛው ተልዕኮ ይዘቱ እውነት የሆነውን ወንጌልን መስበክ ነው—ማቴ. 24፡14፤ ኤፌ. 1፡13፤ ቆላ. 1፡5።
2. እውነትን መስበካችን የከፍተኛው ወንጌል መሰበክ ነው—ማር. 16፡15፤ 1 ጢሞ. 2፡4።
3. የእግዚአብሔር ወንጌል ከፍተኛው ነጥብ፣ በሕይወት እና በባሕርይ ተመላኪነቱን ሳይጨምር ሰው አምላክ ይሆን ዘንድ አምላክ ሰው መሆኑ ነው—ሮሜ 1፡3-4፤ 8፡3፣ 29።

ለ. ለአማኞች ብቻ ሳይሆን ለማያምኑት ጭምር እውነትን እናሰራጭ ዘንድ ጌታ ውድ የሆነውን የራሱን እውነት ሰጥቶናል፤ በምድር ላይ እያንዳንዱ ሰው እውነቱን መስማት ያስፈልገዋል—ዮሐ. 18፡37።

ሐ. የአሁኑ ዘመን ይጠናቀቅ ዘንድ ጌታ እንድንሄድ እና አሕዛብን ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ አዞናል—ማቴ. 28፡19-20።

መ. እውነትን በመማር፣ እውነትን በመተግበር፣ እውነትን በመናገር እና እውነትን በማሰራጨት ከጌታ ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—ዘካ. 8፡16።

ሠ. ዛሬ የጌታን ምለሳ ለማሰራጨት ከወደድን፣ የእውነትን እያንዳንዱ ገጽታ ማወቅ እና እውነቱን ማብራራት መቻል አለብን—2 ቆሮ. 4፡2፤ 3 ዮሐ. 3-4፣ 8።

ረ. የመለኮታዊ እውነቶች መሠራጨት የጌታን የማደስ ዘመን ያመጣል፤ በኢሳይያስ 11፡9 መሠረት "ውኃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለችና" ከዚህ የተነሣ ተሃድሶው ይመጣል።

© 2021 Living Stream Ministry